# <u>ታላቅ የህዝብ ስብሰባ ጥሪ</u>

## ለሀገር ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያውያን በሙሉ።

ያገራችን የፖለቲካ ቀውስና ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ የሄደው የሰብአዊ መብት ረገጣ ፣ ያካባቢ ሀገሮችንና አልፎ ተርፎም የዓለምአቀፍ ህብረተሰብ ትኩረትን ከሳበ ሶስት አሰርተ ዐመታት በላይ አስቆጥሯል ።

የደርግ መንግሥት በአዋጅ ቀይ ሽብር የሚል መጠሪያ ሰጥቶ ፣ በህዝባችን ላይ ያካሄደው ጭፍጨፋ ቁስል ሳይድንና የፈሰሰው ደም ሳይደርቅ ፣ ደርግን የተካው ጎሰኛው ፋሺስት ህዋሀት / ኢህአዴግ ፣ ለፋሺስታዊ ተግባሩ ስም ባይሰጥም፤ በዘር፣ በቋንቋና በሀይማኖት ከፋፍሎ እጅግ አሰቃቂ የሆነ ጭፍጨፋ፣ የዘር ማጥፋት ወንጀልና አገር የማፈራረስ ተልዕኮውን እየፈፀመ ነው።

ከዛሬ 35 ዓመት በፊት የተነሱት የዴሞክራሲ፣ የሰብዓዊና የዜግነት መብት ጥያቄዎች ፣ ዛሬም መልስ አላገኙም። ዛሬም ልጆች በወላጆቻቸው ፊት ፤ ወላጆችም በልጆቻቸው ፊት ይገደላሉ። ህዝብ የመረጣቸው ተወካዮች፣ የሰብዓዊ መብት ታጋዮችና የሲቪክ ማህበራት መሪዎች፣ ታሥረዋል፣ ተሰደዋል። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ ለነዚህ ግፈኛ ገዢዎች ፣ አሜን ብሎ የተገዛበት ጊዜ አልነበረም ።

በዚህ ረጅም ህዝባዊ ትግል ውስጥ፣ ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ ዛሬ በዓላማቸው ፀንተው፣ ከሶስት አሥርተ ዓመታት በላይ፣ ጨቋኞችን፣ አምባገነኖችንና ጎሰኛ ፋሺስቶችን በመታገል፣ ከፍተኛ የትግል ልምድ ያላቸው፣ <u>አቶ ኢያሱ ዓለማየሁ</u> ፣ የኢህአፓ ከፍተኛ አመራር አባል፣ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ፣ የዴሞክራሲያዊ ትግል ስልትና ስትራተጂ በተመለከተ ፡ ሰፋ ያለ ገለፃ ያደርጋሉ ።

ስለዚህም ፣ በፐርዝና በአካባቢዋ የምትገኙ ኢትዮጵያውያን በሙሉ በዚህ ታላቅ ስብሰባ ተካፋይ ትሆኑ ዘንድ ጥሪያችንን በትህትና እናቀርባለን ።

የስብሰባው ቀን ፤----11 **Feb 2007**
ሰዓት ፤--- 4፡30 pm

ቦታው **Morley Sport and Recreation Center**
**Corner of Wellington and Mangini Streets**
**Morley, W.A.,** 6062

የኢትዮጵያ ህዝብ ያሸንፋል !!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፎረም ሥራ አመራር ኮሚቴ ።